ተሀድሶውና መጪው ጊዜ

ታከለ አለሙ

መንግስት በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴውን በሀገራዊ ደረጃ እያካሄደ ይገኛል፡፡ የጥልቅ ተሀድሶ ግምገማው በአመራሩ ዘንድ ያለው የአመለካከት ክፍተት መቀረፍ እንዳለበት፤ አመራሩ በውጤታማነት መመዘን እና ብቃትና ችሎታ ያለው ሰው በተገቢው ቦታ መመደብ እንደሚገባው ግንዛቤ ተይዞ እየተካሄደ ነው፡፡ ከተሀድሶው ጎን ለጎን ተፈጥሮ የነበረውን የሰላም እጦትና አለመረጋጋት ለመቆጣጠር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ በሀገሪቱ ላይ ሊያመጣና ሊያስከትል ይችል የነበረውን የከፋ አደጋ እንዲከላ አድርጎአል፡፡

በእርግጥ የምንግዜም የሀገሩ ሰላም ዋስትና ሕዝብ ነው፡፡ ሰላሙንም የጠበቀው ሕዝብ ነው፡፡ በተወሰነ ወቅት ድፍርሶ የነበረውን ሁኔታ እንዲረጋጋ በማድረግ በኩል ህዝቡ የተጫወተው ሚና ቀላል አይደለም። አንዳንድ አክራሪና ጽንፈኛ ሀይሎች ሊፈጥሩት የነበረውን ጥፋት መከላከልና ማስቀረት የቻለውም ሕዝብ ነው፡፡

የተሀድሶው መሰረታዊ አላማ ጉድለቶችን በመሰረታዊነት በመቅረፍና በማስወገድ የተጀመሩትን ሀገራዊ የለውጥና የልማት እድገቶች በማስቀጠል ከግብ ማድረስ ነው፡፡ በሁሉም መስክ ሰፊ ጉድለቶችና አስቸጋሪ ተብለው የሚጠቀሱ አደናቃፊ ሁኔታዎች መከሰታቸውን በውል ያጤነው የተሀድሶው እንቅስቃሴ በተለያዩ ደረጃዎች የሚጠቀሱ በመንግስት አሰራርና አመራር ውስጥ የታዩ ብልሹ አሰራሮችን ነቅሶ በማውጣትና እርምጃ በመውሰድ የሕዝቡን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመፍታት በሚያስችል ደረጃ እየሰራ ይገኛል፡፡

ሙስና፣ ኪራይሰብሳቢነት፣ የመልካም አስተዳደርና የፍትሕ ችግር አድገውና ገዝፈው የሕዝብ ንቅናቄን የወለዱት በሕዝቡ ውስጥ መከፋትና ምሬትን በማስከተላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሕዝቡን እንዲያገለግሉ የተሾሙት ግለሰቦች ሕዝብና መንግስትን ሆድና ጀርባ በማድረግ ሕዝቡ እንዲከፋ መሰረታዊ ምክንያት መሆናቸው በበቂ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ ይህ አይነቱ ብልሹ አሰራር ዳግም እንዳይመለስ አሁንም ጠንክሮ መስራትና የተለያዩ የቁጥጥር ዘዴዎችና አሰራሮችን መፍጠር ይጠይቃል፡፡

የሌብነትና የዘረፋ ምንጩ በመንግስት የኃላፊነት ቦታ የተመደቡ ሰዎች ከኪራይ ሰባሳቢዎችና ከሙሰኞች ጋር ያላቸውን ቁርኝትና ትስስር እስካላቆሙ ድረስ  አይደርቅም፡፡ ለመንግስትም ለሕዝብም ትልቁ ችግርና አሳሳቢ ሁኖ የኖረው ወደፊትም ትልቅ ጥንቃቄ የሚጠይቀው ጉዳይም ይህው ነው፡፡ ባልሰሩበት መክበርና የበርካታ ሀብቶች ባለቤት መሆን መሻት ያስከተለውን አደጋ ሁሉም ወገን አይቶታል፡፡ ዳግም ይደገም ዘንድ የሚፈቅድ ማንም የለም፡፡

ተሀድሶው ያተኮረው በመሰረታዊነት ከሕዝብ ለቀረቡ በርካታ ጥያቄዎች በየደረጃው መልስ ለመስጠት ሲሆን ችግሮችም ደረጃ በደረጃ እንደሚፈቱ ይታመናል፡፡ ጥያቄዎቹ ካልተፈቱ ግን ሌላ ዙር ውጥንቅጥ እንዳያመጡ ከወዲሁ ሊታሰብበት የሚገባ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ በርግጥ የአመራሮች መለዋወጥ በብዙ ቦታዎች ተካሂዶአል፡፡ መልካም ጅምር ነው፡፡ ይህ ብቻ ግን ችግሩን አይፈታውም፤ ብዙ ሊፈቱ የሚገባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡

የተሻለ ሀገራዊና ሕዝባዊ አገልግሎት ከመስጠት አንፃር በሲቪል ሰርቫንቱ ውስጥ የተሀድሶውን መንፈስ ለማስረጽ የተካሄዱት ንቅናቄዎች የተሻለ ግንዛቤ እንደፈጠሩ ይታመናል፡፡ ይህንን ጅምር በተሻለ ሁኔታ ለማስቀጠል ስራዎች ሁሉ በቅጡ ተለይተው በባለሞያዎች  እንዲሰሩ ማድረግ ለተሻለ ለውጥ ያበቃል፡፡

ተሀድሶው በመላው ሀገሪቱ በስፋት እየተካሄደ ሲሆን ሁሉንም የስራ መስኮች ጥንካሬና ደካማ ጎን፣ የአመራሩን ክፍተት፣ ብቃትና የችሎታ ሁኔታ በመለየት የበለጠና የተሻለ ስራ መስራት በሚቻልበት ደረጃ ላይ የአሰራርና የአመራር ለውጦችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ሰፊ ሀገራዊና ሕዝብን መሰረት ያደረገ የለውጥ ስራዎችን ለመስራት የሚደረገውን ታላቅ ርብርብ ያህል ብዙ ፈተናዎችና መሰናክሎች መኖራቸውን መካድ አይቻልም፡፡ ትልቁ የአመራር ብቃትና ወሳኝነት የሚለካውና የሚፈተሸው የተከሰቱ ችግሮችን በመለየትና በመተንተን፤ እንዲሁም መፍትሄዎቻቸውን ለይቶ በማስቀመጥ ወደስራ በመግባት ነው፡፡

ሀገሪቱ እያካሄደች ካለችው ሰፊ የመሰረተ ልማት ግንባታ አንጻር አብሮ የተከሰተው ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት በአጭር ግዜ ይፈታል ተብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡ እንደውም የተሀድሶው ለውጥና እንቅስቃሴ እየተካሄደ ባለበትም በዚህ ሰአት በብዙ መስኮች ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነቱ ጎልብቶ በመካሄድ ላይ መሆኑን የሕዝብ አስተያየቶች ይጠቁማሉ፡፡

ተሀድሶው ተጀመረ ማለት ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን ቆርጦ ለመታገል ወሳኝ እርምጃዎች አስፈላጊ መሆናቸውን የሚያመላክት እንጂ ችግሩ ቆሟል ማለት አይደለም፡፡ ይሄ የሚያሳየው በጅምር መንግስታዊ እርምጃዎቹ ያልተነካው ሙሰኛና ኪራይ ሰብሳቢው ሀይል ስልቱንና ዘዴውን ቀይሮ ተሀድሶውን እየዘመረ ከጀርባ ዝርፊያውንና ዋልጌነቱን ቀጥሎአል ማለት ነው፡፡

መንግስት የወሰደው ወሳኝ እርምጃ አይደለም የሚሉም በርካታ አስተያየቶች አሉ፡፡ ለምን? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የመንግስትና የመንግስት ብቻ ይሆናል፡፡ ከሕዝብ ጥቆማ ከመጠየቅ ይልቅ  መንግስት በራሱ እጅ በርካታ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉት አይደለም ወይ? ከመንግስትስ የተሰወረው ምንድነው፣ ለምን እርምጃ አይወስድም? የሚሉሉ የሕዝብ አስተያየቶችም በስፋት ይደመጣል፡፡ ተፈራርቶ

የሚኬድበት የመጠባበቅ መንገድ ሀገሪቱንና ሕዝቡን ውስብስብ ችግር ውስጥ እንዳይከታቸው መንግስት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል፡፡

በግንባታው ዘርፍ፣ በተለይም በሜጋ ፕሮጀክቶች አካባቢ ሲካሄድ የነበረው ሙስና፣ የኪራይ ሰብሳቢዎች ሴራና መመሳጠር ዛሬስ ምን መቆጣጠሪያ ልጓም ተበጀለት? ወይንስ እንዳሻቸው እየፈነጩበት ይገኛሉ? ለሚሉት የሕዝቡ ጥያቄዎች ተሀድሶው ወሳኝ መልሶችን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ካልሆነ “መጪው ጊዜ ከኢህአዴግ ጋር ብሩህ ነው” የሚለውን ጥያቄ ምልክት ስር ሊጥለው ይችላል።

ፕሮጀክቶች ያለሕጉና ያለስርአቱ ያለጨረታ በከፍተኛ ባለስልጣናት ትእዛዝ ትላንት ሲሰጡ  የነበረበት ሁኔታ ዛሬስ ለውጥና መሻሻል አምጥቶአል ወይንስ ባለበት ቀጥሎአል ሚለውም ጥያቄ ይነሳል፡፡ በስራ ሀላፊዎችም ሆነ ተሿሚዎች በስፋት የሚስተዋለው ችግር የአመለካከት እና የአቅም ማነስ ችግር ብቻም አይደለም፤ የተደራጀ ሌብነትም ጭምር ነው፡፡ ይህ ለመንግስት ትልቅ ፈተና ቢሆንም ሊጋፈጠውና መፍትሄ ሊያስገኝለት ግድ ይለዋል፡፡

ሜጋ ፕሮጀክቶች የሚጓተቱበት መሰረታዊ ምክንያትም ሌላ ብዙ ሰበብ ከመስጠት ይልቅ ይሀው የሙሰኛውና የኪራይ ሰብሳቢው ጨዋታ መሆኑን ማወቁ ተገቢ ነው፤ እያዘገዩ፣ ምክንያት እየፈጠሩና ስራውን እያጓተቱ ተጨማሪ በጀትና ገንዘብ እየጠየቁ የመንግስትና የሕዝብን ሀብት መዝረፍን የተካኑ ወገኖች ስለመኖራቸው አሌ የሚል የለምና።

ባጠቃላይ፣ መንግስት በሁሉም አቅጣጫ አይኑን ሊጥል፣ አሰራሩን ሊፈትሽ፣ በአጥፊዎች ላይ የማያዳግም እርምጃን ሊወስድ የግድ ሲሆን የተሃድሶውን ትሩፋቶች ለህዝብ ለማሳየትም ቆርጦ መነሳት ያለበት ወቅት ላይ መሆኑን ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋው አይገባም፤ ከተሀድሶው በኋላ ያለው መጪው ጊዜም ምን ያህል ብሩህ እንደሆነም ከወዲሁ ሊነግረን ይገባል።